# አልተገናኙቶ

(በሕያዉ ቃል)

ቋንቋ ሀብትነቱ፣

ሰዉን ማግባባቱ፣

ምርቂን ከፍትፍቱ፤

ለይቶ አበጥሮ፣

የሃሳብን ፍሬ ከመሰል ገለባ፣

እሾሁን ከአበባ፤

አእምሮን ማናበብ፣

በቃላት ቅርርብ፣

በሰዋሰዉ ስምም በሀረጎች ትዉስብ፣

ሊያዛምድ ሊያግባባ፣

ሊያስታጥቅ በጋራ፣

ለቀጣዩ ትግል - ለማይቀረዉ ሥራ፤

ነበር ከጠዋቱ ጥንት አፈጣጠሩ፣

ማብራራት ማድርጀት፡ የማንቃት ቀመሩ፤

ግን ዘመን ሲደረጅ ትዉልድ ያረጅና፣

ስር ይይዛል ሲባል፣

ጥበበ አመክንዮ ራሱ ይመክንና፤

ይጠመዳል መሰል፣

አገር ከነሕዝቡ ተርታ እንደወሬ፣

በገዛ ብርብራዉ በከተረዉ ኩሬ፤

አንድምታ ትርጓሜዉ ቅጥአምባሩን አጥቶ፣

ብያኔዉም ከፍቶ፣

የጊዜአችን ቋንቋ ከሚናዉ ተፋርሷል፣

እንኩዋንስ ሊያስማማ መስማሚያዉ ጠፍቶታል፡፡

በዘመኑ ዘዬ በ”ሥልጡኖች” መስመር፣

ባይተዋሮች ናቸዉ መርህና ተግባር፣

አይተዋወቁም ቃልኪዳን ከፍቅር፣

ደግሞም ስነምግባር ከዓላማና ክብር፤

ጽናት “የፋራ” ነዉ፣ ጀግንነት የገልቱ፣

ሥር መንቀል ለምኑ?! ጥገና ነዉ ለዉጡ፤

“ድርጅት” ጨረባ ተቧድኖ አተካሮ፣

በሰዉ መንጋ አጀብ በፌሽታዉ ተሳክሮ፣

ጉንጉን ጽጌ ካንገት በአደይ ንስንስ አምሮ፤

ግዳይ ሳያስቆጥር፣

ድል መለኪያዉ ሆታ የሚንር ከበሮ፡፡

በዘመነኞቹ ስልት “አራዳኛ” መንፈስ፣

“ፖለቲካ” — “ሥራ” -የሊቃዉንት “ቢዝነስ”፣

“በትርፋማ ምርጫ”፣ “ምክር-ቤት” መዘፍዘፍ፣

ድግሪ ነዉ “ሊቼንሳዉ”፣

ማራ’ ዝንብ - አንደበት -ዲስኩር ማሻሻጫዉ፣

“ቱሪናፋ” ስልቱ፣ ገደብ የለሽ ጉራ፣

እንደ “ቺፖሊኒ”፣ ወይ “መሎቲ” ቢራ፣

“መረብን በቅትል” —“ጦር ካሻኝ ከአስመራ”፣

ደህንነት መዝሙሩ፣

እንደ ገዛ ራሱ፣ ጠላቱን አፍቅሮ፣

ከስርዐት “ መቻቻል “ - ሕጎቹን አክብሮ፣

“ሰላማዊ  አመጹ”--የሌለዉ ኮሽታ፣

በተፈቀደ ሰልፍ፣  በፈቃድ እምቢታ፣

ቀን ካወገዙት ጋር፣ ማታ እየተሻሹ፣

እንደ ቅልብ ጠቦት፣

ያ’ ላማጁን ጌታ መዳፍ እየላሱ፣

በአዲሱ ቋንቋ፣

“መገንጠል-መብት  ነዉ - በዐንቀጽ የረቀቀ፣

እንዳሻ ‘ሚቸሩት፣  “ድንበር “ ለጠየቀ፣

ትግልም ወኔ አይሻ፣ የተትረፈረፈ፣

አረቄ ከጫረዉ፣  ሞቅታ ያለፈ፡፡”

እንዲል ተጻፈና፣ ከቶ አልተገናኘቶ፣

በ”ሥልጡኖች” መዝገብ፣ ቃል ሐዲዱን ስቶ፣

እንደ ስናየር ግምብ፣ ሰማይ ጠቀስ ሥራ፣

ጡብ ስንል አሸዋ፣ ዉሃ ስንል ኖራ፤

አረፍነዉ ሆነና፣

ነገረ ሥራችን፣ ቢታጠብ አይጠራ፣

እንኩዋን ሊፈነጥቅ፣ የተስፋችን ጮራ፣

የመከራችን ዶፍ፣ ዘንቦም አላባራ።

መስከረም፣ 2002